መመሪያ ቁጥር 1081/2017
ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራምን ለመወሰን የወጣ

Directive Number 1081/2025
Issued to Determine the Authorized Economic Operators Program with Special Privilege

ከዓለም የጉምሩኮች ድርጅት የንግድ ማሳለጥ እና ደህንነት ማዕቀፍ (SAFE Framework of Standards) ስታንዳርድ ጋር የተጣጣመ ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም በመቅረጽ ተግባራዊ ማድረግ በማስፈለጉ፤

WHEREAS, Ethiopia is required to formulate and implement an Authorized Economic Operators (AEO) Program with Special Privilege aligned with the World Customs Organization's SAFE Framework of Standards to enhance trade facilitation and security;

በአለም አቀፍ ንግድ እና በአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ ተሳትፎ ያለው ሰው በተቀመጡ መስፈርቶች መሰረት እየተመዘነ ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም የሚታቀፍበትን እና የሚተዳደርበትን አሰራር ለመወሰን በማስፈለጉ፤

WHEREAS, There is a need to determine the procedures in which individual participating in international trade and supply chains, after being evaluated based on established criteria, become inrolled and managed in/under specially authorized economic operators program;

ከፍተኛ ስጋት ያላቸውን ጭነቶች የመለየት አቅምን በማሻሻል እና በጉምሩክ አስተዳደሮች መካከል ያለውን ትብብር በማጠናከር ደህንነቱ የተጠበቀ አለማቀፍ የሸቀጦች ፍሰትን የሚያበረታታ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

WHEREAS, There is a need to enhance the capacity to identify high-risk cargo and strengthen cooperation among customs administrations to promote a secure international flow of goods;

ለሕግ ተገዥ የሆኑትን በማበረታታት ለንግድ፣ ለአምራች ኢንዱስትሪው እና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ቀለል ያለ፣ ፍትሐዊ፤ ፈጣን እና ተገማች የጉምሩክ አገልግሎት በመስጠት የኢኮኖሚ ልማትን መደገፍ በማስፈለጉ፤

WHEREAS, the need to support economic development by encouraging compliance with the law, creating favorable conditions for trade, manufacturing, and investment through simple, just, fast, and predictable (uniform) customs services;

በንግዱ ማህበረሰብ እና በመንግስት ተቋማት መካከል አጋርነት እና መተማመንን

WHEREAS, the need to implement a system that strengthens partnership and trust between

በማጠናከር የአገራችን ኢኮኖሚ እንዲጎለብት የሚያደርግ ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የገቢዎች ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 180 (2) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

the business community and government institutions to enhance the country's economy;

Now, therefore, The Ministry of Revenues has issued this Directive pursuant to the authority granted under Article 180(2) of the Customs Proclamation No. 859/2014 (as amended).

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራምን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1081/2017 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል፦

1) "ልዩ መብት የተፈቀደለት የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ" ማለት በአለም አቀፍ የአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ ሰው በአለም የጉምሩኮች ድርጅት የንግድ ማሳለጥ እና ደህንነት ማዕቀፍ (SAFE Framework of Standards) ስታንዳርድ የተዘጋጀውን መስፈርት አሟልቶ ለተገኘ የመብቱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል የማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በኮሚሽኑ የተሰጠው ሰው ነው።

2) "ፕሮግራም" ማለት ልዩ መብት የተፈቀደለት የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ሰው የቅድሚያ እና ፈጣን አገልግሎት እንዲያገኝ የሚታቀፍበት አሰራር ነው።

3) "የምስክር ወረቀት" ማለት በደንቡና በዚህ መመሪያ የተቀመጠውን መስፈርት አሟልቶ

Part One

General Provisions

1. Short Title

This Directive may be cited as the Authorized Economic Operators Program Directive No. 1081/2025, issued to establish the program for authorized economic operators.

2. Definitions

For the purpose of implementing this directive:

1) "Authorized Economic Operator" means a person participating in the international supply chain who has met the standards set by the World Customs Organization's SAFE Framework of Standards for trade facilitation and security, and has been issued a certificate of authorization by the Commission to benefit from the rights.

2) "Program" means the process through which an authorized economic operator receives priority and expedited services.

3) "Certificate" means the authorization issued by the Commission to a person who meets the requirements set by the regulation and this

የመብቱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል በኮሚሽኑ የሚሰጥ ማረጋገጫ ነው።

directive to benefit from the rights.

4) "በራስ የሚደረግ ግምገማ" ማለት በልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም ለመታቀፍ የሚያመለክት ሰው በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መመዘኛ መስፈርቶችን ስለማሟላቱ የውስጥ አሰራሩን ገምግሞ ለኮሚሽኑ የሚያሳውቅበት ሥርዓት ነው።

4) "Self-Assessment" means the system by which a person applying for the Authorized Economic Operators Program evaluates their internal processes to confirm compliance with the criteria set by this directive and reports to the Commission.

5) “ኦዲት” ማለት በፕሮግራሙ ለመታቀፍ የሚያመለክት አዲስ ወይም ነባር ሰው መስፈርቱን ስለማሟላቱ በኮሚሽኑ የሚከናወን የማረጋገጥ ተግባር ነው።

5) "Audit" means the verification process conducted by the Commission to confirm that a new applicant or existing individual for the program meets the required standards.

6) “ሚኒስቴር እና ሚኒስትር” ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የገቢዎች ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው።

6) "Ministry and Minister" mean the Ministry of Revenues and the Minister, respectively.

7) “ኮሚሽን እና ኮሚሽነር” ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን እና የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ነው።

7) "Commission and Commissioner" mean the Ethiopian Customs Commission and the Commissioner of the Commission, respectively.

8) “አዋጅ” ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 እና የተሻሻለው የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 1160/2011 ነው።

8) "Proclamation" means the Customs Proclamation No. 859/2014 and the amended Customs Proclamation No. 1160/2019.

9) “ደንብ” ማለት የጉምሩክ ደንብ ቁጥር 518/2014 ነው።

9) "Regulation" means the Customs Regulation No. 518/2022.

10) “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ መብት የተሰጠው ሰው ነው።

10) "Person" means a natural person or a person granted rights by law.

11) በዚህ መመሪያ ትርጉም ያልተሰጣቸው ሌሎች ቃላቶች እና ሐረጎች በአዋጁ እና በደንቡ ያላቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

11) Other words and phrases not defined in this directive shall have the meanings assigned to them in the Proclamation and Regulation.

3. ዓላማ

3. Objective

ከአለም የጉምሩኮች ድርጅት የደህንነት እና

To design and implement an Authorized

ንግድ ማሳለጥ ማዕቀፍ ስታንዳርዶች ጋር የተጣጣመ ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም ቀርጸ ተግባራዊ ማድረግ ነው።

4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ልዩ መብት በተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም ለመታቀፍ አዲስ ለኮሚሽኑ ጥያቄ በሚያቀርብ እና የተዘጋጀውን መስፈርት አሟልቶ በፕሮግራሙ የታቀፈ ሰው ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

ክፍል ሁለት

በራስ የሚደረግ ግምገማ፣ ኦዲት እና መመዘኛ መስፈርት

5. በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ማመልከት የሚችሉ አካላት

1) አስመጪ፤
2) አምራች፤
3) ላኪ፤
4) የዕቃ አስተላላፊ፤
5) የጉምሩክ አስተላላፊ፤
6) የመጋዘን ባለቤት፤
7) የዕቃ አጓጓዥ፣
8) የጭነት አቀናጅ፤
9) ሌሎች በንግድ የአቅርቦት ሰንሰለት ተሳትፎ ያላቸው።
10) በዚህ መመሪያ አንቀፅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በፕሮግራሙ እንዲታቀፉ ልዩ ድጋፍ ያደርጋል፤ በልዩ ሁኔታም በፕሮግራሙ

Economic Operators Program in line with the World Customs Organization's SAFE Framework of Standards for security and trade facilitation.

4. Scope of Application

This Directive shall apply to any person who submits a new application to the Commission for inclusion in the Authorized Economic Operators Program and who meets the established requirements and is included in the program.

Section Two

Self-Assessment, Audit, and Evaluation Critera

5. Entities Eligible to Apply for the Program

1) Importer;
2) Manufacturer;
3) Exporter;
4) Freight Forwarder;
5) Transitor;
6) Warehouse Owner;
7) Transporter of Goods;
8) Freight Coordinator;
9) Others involved in the commercial supply chain.
10) Notwithstanding the provisions in Article (5), the Commission shall provide special support to micro, small, and medium enterprises to participate in the program and facilitate their inclusion under special conditions.

የሚታቀፉበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

6. በራስ ስለሚደረግ ግምገማ መስፈርቶች

ለአስመጪ፣ ለላኪ እና ለአምራች

ሀ) በአስመጪነት፣ በአምራችነት እና በላኪነት ዘርፍ የተመዘገበ ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ ያለው፤

ለ) አመልካቹ አስመጪ የሆነ እንደሆነ ሶስት /3/ ዓመት እና ከዚያ በላይ፤ እንዲሁም አምራች ወይም ላኪ የሆነ እንደሆነ ሁለት /2/ ዓመት እና ከዚያ በላይ በስራ ላይ የቆየ መሆን አለበት፤

ሐ) አመልካቹ በጉምሩክ ያለው የስጋት ደረጃ ቢያንስ መካከለኛ ማለትም ቢጫ የስጋት ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆን አለበት፤

መ) አመልካቹ ባለፉት ተከታታይ ሶስት ዓመታት ወደ አገር ውስጥ ባስገባው ዕቃ ላይ በራስ አነሳሽነት አሳውቆ የከፈለው የቀረጥና ታክስ መጠን በጠቅላላ ከከፈለው ከ85 በመቶ ማነስ የለበትም፤

ሠ) አመልካቹ ባለፉት ተከታታይ ሶስት ዓመታት በማናቸውም ሁኔታ በኢኮኖሚ ወንጀል ያልተከሰሰ ወይም ተከሶ የጥፋተኝነት ውሳኔ ተወስኖበት ቅጣቱን ካጠናቀቀ ሶስት ዓመት ያለፈው፤

ለጉምሩክ አስተላላፊ እና ለዕቃ አስተላላፊ

ሀ) በጉምሩክ አስተላላፊነት ወይም በዕቃ አስተላላፊነት ዘርፍ የተመዘገበ ሕጋዊ የንግድ

6. Self-Assessment Criteria

1) For Importers, Exporters, and Manufacturers

a) Must have a legally registered business license in importing, manufacturing, or exporting;

b) The applicant, to be included in the program, must have been operational for at least three (3) years as an importer, or two (2) years as a manufacturer or exporter;

c) The applicant's customs risk level must be at least medium, i.e., yellow risk level;

d) The applicant must have voluntarily declared and paid duties and taxes on imported goods over the past three consecutive years, with the total amount paid not less than 85% of the total assessed;

e) The applicant must not have been charged with an economic crime in the past three consecutive years, or if charged and convicted, three years must have passed since completing the penalty.

2) **For Custom Transitors and Freight Forwarders**

a) Must have a legally registered business license in customs transit or freight

ፈቃድ ያለው፤

ለ) አመልካቹ በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ከ3 ዓመት በላይ በዚሁ የጉምሩክ ወይም/እና የዕቃ አስተላላፊነት መስክ በስራ ላይ የቆየ መሆን አለበት፤

ሐ) አመልካቹ በጉምሩክ ያለው የስጋት ደረጃ ቢያንስ መካከለኛ ማለትም ቢጫ የስጋት ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆን አለበት፤

መ) አመልካቹ ባለፉት ሶስት ዓመታት ወደ አገር ውስጥ ለገቡ ዕቃዎች ዲክሌር ባደረጋቸው ሰነዶች ላይ ያለ ልዩነት የተከፈለው የቀረጥና ታክስ መጠን በጠቅላላ ከተከፈለው ከ85 በመቶ ማነስ የለበትም፤

ሠ) ባለፉት ሶስት ዓመታት በማናቸውም ሁኔታ በኢኮኖሚ ወንጀል ያልተከሰሰ ወይም ተከሶ የጥፋተኝነት ውሳኔ ተወስኖበት ቅጣቱን ካጠናቀቀ ሶስት ዓመት ያለፈው፤

የመጋዘን ባለቤት፣ የጭነት አቀናጅ እና የዕቃ አጓጓዥ

ሀ) በጭነት አቀናጅነት እና በዕቃ አጓጓዥነት ዘርፍ የተመዘገበ ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ ያለው፤

ለ) አመልካቹ በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ከ3 ዓመት በላይ በስራ ላይ የቆየ መሆን አለበት፤

ሐ) አመልካቹ ባለፉት ሶስት ዓመታት በማናቸውም ሁኔታ በኢኮኖሚ ወንጀል ያልተከሰሰ ወይም ተከሶ የጥፋተኝነት ውሳኔ ተወስኖበት ቅጣቱን ካጠናቀቀ ሶስት ዓመት ያለፈው፤

በዚህ አንቀፅ የተደነገገው ቢኖርም የቅድመ

forwarding;

b) The applicant must have been operational in customs transit or freight forwarding for more than three (3) years;

c) The applicant's customs risk level must be at least medium, i.e., yellow risk level;

d) The applicant must have paid duties and taxes on declared goods over the past three years without discrepancies, with the total amount paid not less than 85% of the total assessed;

e) The applicant must not have been charged with an economic crime in the past three years, or if charged and convicted, three years must have passed since completing the penalty.

3) **For Warehouse Owners, Freight Coordinator, and Transporters**

a) Must have a legally registered business license in cargo arranging or transportation;

b) The applicant must have been operational for more than three (3) years;

c) The applicant must not have been charged with an economic crime in the past three years, or if charged and convicted, three years must have passed since completing the penalty.

4) Notwithstanding the provisions in this

ኦዲት መስፈርቱን ባለማሟላቱ ማመልከቻው ተቀባይነት ያጣን ሰው ኮሚሽነሩ ሲያምን የቅድመ ኦዲት መስፈርቱን እንዲያልፍ ሊፈቅድ ይችላል፤

article, if an applicant's application is rejected for failing to meet pre-audit requirements, the Commissioner may, at his (her) discretion, allow the applicant to meet the pre-audit requirements.

7. ስለማመልከቻ አቀራረብ እና ተቀባይነት ስለማግኘት

7. About Application Submission and Acceptance

1) ማንኛውም በፕሮግራሙ ለመታቀፍ የሚያመለክት ሰው በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 ላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን አሟልቶ ኮሚሽኑ ለዚሁ ዓላማ ባዘጋጀው የቴክኖሎጂ ሥርዓት በመጠቀም ወይም የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት ማቅረብ ይኖርበታል።

1) Any person applying to participate in the program must meet the requirements outlined in Article 7 of this directive and submit an application using the Commission's technology system or by filling out an application form.

2) ኮሚሽኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት የቀረበውን ማመልከቻ ስለመቀበሉ ማመልከቻው በቀረበለት በአንድ ቀን ጊዜ ገደብ ውስጥ ማረጋገጥ ይኖርበታል።

2) The Commission must verify the acceptance of the application submitted under sub-article (1) within one day of its submission.

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት የቀረበው ማመልከቻ በመመሪያው የተቀመጡ የቅድመ ኦዲት መስፈርቶች ስለመሟላታቸው በማረጋገጥ ማመልከቻውን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በአስራ አራት /14/ የሥራ ቀናት ውስጥ የቴክኖሎጂ ሥርዓት በመጠቀም ምላሽ ይሰጣል።

3) The application submitted under sub-article (1) will be checked for compliance with the pre-audit requirements of the directive, and a response will be provided within 14 working days from the date of receipt using the technology system.

8. በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች

8.Eligibility Requirements for Program Participation

1) ኮሚሽኑ በአንቀፅ 8 መሰረት የቅድመ ኦዲት መስፈርቶችን አሟልቶ ተቀባይነት ያገኘውን ሰው በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ብቁ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የሕግ ተገዥነትና የውስጥ አሰራር ኦዲት

1) The Commission will conduct a legal compliance and internal procedure audit to confirm the eligibility of a person who has met the pre-audit requirements under Article 8 for program participation.

ያከናውናል።

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት በኮሚሽኑ የሚከናወነው የኦዲት ሥራ የሚከተሉትን ዋና ዋና መስፈርቶች መሰረት ያደረገ ይሆናል። ሀ) በጉምሩክ እና በአገር ውስጥ ገቢ ያለው የሕግ ተገዥነት ሁኔታ ለ) ለአገር ኢኮኖሚ የሚያደርገው አስተዋፅኦ ሐ) የሃብት አመራር እና የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት መ) የመረጃ ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ሁኔታ ሠ) የፋይናንስ አቅም ረ) የጥንቃቄና ደህንነት መስፈርቶች

2) The audit conducted by the Commission under sub-article (1) will be based on the following main criteria: a) Compliance with customs and domestic revenue laws b) Contribution to the national economy c) Resource management and internal control system d) Information technology infrastructure status e) Financial capacity f) Safety and security requirements

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተቀመጡ ዋና ዋና መመዘኛዎች ስለመሟላታቸው ለማረጋገጥ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ተቀፅላ (Annex) ውስጥ የተቀመጡ መስፈርቶችን በመጠቀም ውጤት ይሰጣል።

3) To ensure compliance with the main criteria under sub-article (2), it will provide/assign a result using the requirements listed in the Annex attached to this directive.

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት በኮሚሽኑ በሚዘጋጅ ዝርዝር የመመዘኛ መስፈርት መሰረት ተመዝኖ 80% እና በላይ ውጤት ያስመዘገበ ሰው በፕሮግራሙ እንዲታቀፍ ይደረጋል።

4) It declares that a person scoring 80% or above, based on the detailed criteria prepared by the Commission under sub-article (3), eligible to participate in the program.

9. የፕሮግራሙ ደረጃዎች

9. Levels of the Program

1) በዚህ መመሪያ አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ (4) ውጤት መሰረት በፕሮግራሙ የሚታቀፍ ሰው በሶስት ደረጃዎች ይመደባል። ሀ) የፕላቲኒየም ደረጃ ለ) የወርቅ ደረጃ ሐ) የብር ደረጃ

1) A person eligible for the program under Article 9, sub-article (4) of this directive will be classified into three levels: a) Platinum Level b) Gold Level c) Silver Level Rights.

2) በዚህ መመሪያ በተቀመጡ ዝርዝር መመዘኛ መስፈርቶች ተመዝኖ ከ90 በመቶ በላይ የፕላቲኒየም ደረጃ፤ ከ85.01 እስከ

2) Based on the detailed criteria, a score above 90% qualifies for Platinum Level, 85.01–89.99% for Gold Level, and 80–85% for Silver Level Rights.

89.99 በመቶ የወርቅ ደረጃ እንዲሁም ከ80 እስከ 85 በመቶ የሚያስመዘግብ የብር ደረጃ መብት ያገኛል።

10. ለኦዲት ስለሚቀርብ ማስረጃ

በዚህ መመሪያ የቅድመ ኦዲት መስፈርቶችን አሟልቶ ተቀባይነት ያገኘ ሰው ለሕግ ተገዥነትና የውስጥ አሰራር ኦዲት ለማረጋገጥ ግብዓት የሚሆኑ የሚከተሉትን ማስረጃዎች ማቅረብ ይጠበቅበታል።

1) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ሰርተፊኬት፣ የታደሰ ንግድ ፍቃድ ሰርተፊኬት፣ የመመስረቻና መተዳደሪያ ደንብ (ኮፒ)፣
2) የድርጅቱ መዋቅር፣ ፕሮፋይል፣ የቋሚ እና ኮንትራት ሰራተኞች ብዛት፣
3) ላለፉት ሶስት ተከታታይ ዓመታት በውጪ ኦዲተሮች የተረጋገጠ የሒሳብ ሪፖርት፣
4) የመካከለኛ ወይም የረጅም ጊዜ ዕቅድ፣
5) የፋይናንስ ፖሊሲ/ አሰራር እና የሒሳብ መዝገብ አያያዝ ሥርዓት፣
6) የጥበቃና የደህንነት ፖሊሲ/ አሰራር እና የመጋዘን አስተዳደር አሰራር፣
7) የሰው ሀብት ፖሊሲ/ አሰራር፣
8) የመረጃ ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት አስተዳደር ፖሊሲ/ አሰራር፣
9) ለገቢ ዕቃዎች ዋና ዋና የአቅራቢዎቻቸው ዝርዝር፣
10) የውስጥ አሰራር ጥራት ማረጋገጫ፣
11) የማህበራዊ አስተዋጽኦ ማስረጃዎች፣
12) የአካባቢ ደህንነት አሰራር፣

10. Evidence to be Submitted for Audit

A person who has met the pre-audit requirements and gained acceptance must submit the following evidence as inputs for legal compliance and internal procedure audit:

1) Taxpayer ID certificate, renewed business license certificate, articles and memorandum of association (copy)
2) Organizational structure, profile, number of permanent and contract employees
3) Financial reports audited for the past three consecutive years
4) Medium or long-term plan
5) Financial policy/procedure and accounting record system
6) Safety and security policy/procedure and warehouse management procedure
7) Human resource policy/procedure
8) IT infrastructure management policy/procedure
9) List of main suppliers for imported goods
10) Internal procedure quality assurance
11) Evidence of social contributions
12) Environmental safety procedure,

11. የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ (9) እና (10) መሰረት በፕሮግራሙ እንዲታቀፍ የተመረጠ ሰው ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም ተጠቃሚ መሆኑን የሚገልፅ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ማመልከቻው ለኮሚሽኑ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት አርባ አምስት ቀናት ውስጥ ይሆናል።

3) በዚህ አንቀፅ መሰረት የሚሰጥ የምስክር ወረቀት የሚያገለግለው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለሶስት ዓመት ይሆናል።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚሰጥ የምስክር ወረቀት በአማርኛ እና በእንግለዝኛ ቋንቋ የሚዘጋጅ ሆኖ የሚከተሉትን መረጃዎች ያካተተ ይሆናል፤

ሀ)የኮሚሽኑ እና የፕሮግራሙ አርማ (Logo)፣
ለ) የመብቱ ተጠቃሚነት መለያ ቁጥር፣
ሐ) የመብቱ ተጠቃሚ ስም፣
መ) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣
ሠ) የተሰማራበት የስራ ዘርፍ፣
ረ) የፕሮግራሙ መብት ደረጃ
ሰ) ፊርማ እና ማህተም፣
ሸ) የምስክር ወረቀቱ የተሰጠበት እና የሚያበቃበት ቀን።

5) ኮሚሽኑ በዚህ አንቀፅ መሰረት የሚሰጥ የፕሮግራሙ ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት እንደተጠበቀ ሆኖ የልዩ መብት ተጠቃሚ ለሆነ ሰው ይህንኑ የሚገልፅ በኮሚሽኑ የታተመ ልዩ መታወቂያ ይሰጣል።

6) በዚህ አንቀጽ በተገለጹ ምክንያቶች እና ሁኔታዎች የመብቱ ተጠቃሚዎች ፈቃድ ወይም የምስክር ወረቀት የሚሰጠው

11. Issuance of Certificate

1) A person selected to participate in the program under Articles 9 and 10 will receive a certificate confirming their status as a beneficiary of the Authorized Economic Operators Program.

2) The certificate to be issued pursuant to sub-article (1) of this article will be within 45 days from the date of application submission to the Commission.

3) The certificate issued under this article is valid for three years from the date of issuance.

4) The certificate issued under sub-article (1) of this article will be prepared in Amharic and English and include:

a) Logo of the Commission and program
b) Beneficiary ID number
c) Beneficiary name
d) Taxpayer ID number
e) Business sector
f) The Program's previllage level
g) Signature and seal
h) Issuance and expiry dates of the certificate.

5) In addition to the certificate to be issued by the commission pursuant to this article, the Commission will issue a special ID to the privileged program participant confirming their status as such.

6) The issuance of the beneficiary's license or certificate under this article will be based on the Commissioner's decision and signature.

በኮሚሽነሩ ውሳኔ እና ፊርማ ይሆናል።

12. መብቱ የሚያስገኛቸው ጥቅሞች

1) የብር ደረጃ ያገኘ የመብቱ ተጠቃሚ የሆነ ሰው የሚከተሉትን ጥቅሞች ያገኛል፡-

ሀ) በልዩ የአገልግሎት መስጫ መስኮት የመስተናገድ፤

ለ) በስራ ቦታ ትራንዚት እንዲጠናቀቅ የማድረግ፤

ሐ) በየትኛውም የጉምሩክ አገልግሎት ቅድሚያ እና ፈጣን አገልግሎት የማግኘት፤

መ) የትራንዚት ፈቃድ በደብዳቤ ዋስትና የመስተናገድ፤

ሠ) የቦንድድ መጋዘን ፈቃድ በደብዳቤ ዋስትና የመስተናገድ፤

ረ) በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ የመስተናገድ፤

ሰ) በቅድመ ዕቃ አወጣጥ አገልግሎት የመስተናገድ፤

ሸ) በውስን ሰነዶች እና/ወይም ዋና ሰነድ እስኪቀርብ በደብዳቤ ዋስትና በኮፒ ሰነድ የመስተናገድ፤

ቀ) ዕቃዎችን ለመለየት በሚያስችል ውስን መረጃ ብቻ የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት በማጠናቀቅ ዕቃዎችን መልቀቅ፤

በ) የቀረጥና ታክስ መጠን ቅድመ ክፍያውን በመክፈል ቀሪውን በባንክ/ኢንሹራንስ ዋስትና የድህረ ክፍያ አገልግሎት የማግኘት፤

ተ) ለወጪ ዕቃዎች ጉምሩክ መምጣት ሳያስፈልገው በቀጥታ ከመጋዘን ታሽጎ እንዲላክ አገልግሎት የማግኘት፤

ቸ)ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ

12. Benefits Provided by the Right

1) A person who has obtained Silver status as a beneficiary of the right will receive the following benefits:

a) Service at a designated service window;

b) Facilitating the completion of transit at the workplace;

c) Priority and expedited service at any customs service;

d) Transit permit processed with a letter of guarantee;

e) Bonded warehouse permit processed with a letter of guarantee;

f) Processing with a low risk level;

g) Processing through pre-clearance services;

h) Processing with limited documents or a letter of guarantee using a copy until the original document is provided;

i) Releasing goods by completing customs procedures with limited information sufficient to identify the goods;

j) Paying part of the duties and taxes upfront and settling the remainder with a bank/insurance guarantee for deferred payment services;

k) Exporting goods directly from a warehouse without requiring customs arrival;

l) Using the Authorized Economic Operators

አንቀሳቃሾች ፕሮግራም አርማን (Logo) የመጠቀም፤	program logo;
ነ) ለኦዲት ሲመረጡ አስቀድሞ መረጃ የማግኘት፣	m) Receiving prior information when selected for an audit;
ኘ) ኮሚሽኑ በሚያወጣቸው ሕጎችና አሰራሮች ላይ ተሳታፊ የመሆን፣	n) Participating in the development of laws and procedures issued by the Commission;
አ) ዝርዝራቸው በኮሚሽኑ ድህረ ገፅ እና/ወይም በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሚዲያዎች ላይ ይፋ የመደረግ፣	o) Having details published on the Commission's website and/or other relevant media;
ከ) የስሪት አገር ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በራሱ የማዘጋጀት፣	p) Preparing the Certificate of Origin independently;
ኸ) ፈጣን የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ሥርዓት የመጠቀም፣	q) Using an expedited duties and taxes refund system;
ደ) ለእድሳት የሚከናወኑ ሂደቶች ሳይጠበቅ ዓመታዊ የጉምሩክ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የሚጠበቅባቸውን የአገልግሎት ክፍያ በመፈፀም እድሳት እንዲያገኙ ማድረግ፤	r) Renewing the annual customs competency certification license without waiting for renewal processes by paying the required service fee;
ጀ) በጉምሩክና ታክስ አሰራሮች ላይ ሞጁላር ስልጠና የማግኘት፣	s) Receiving modular training on customs and tax procedures;
ጠ) የ24/7 የጉምሩክ አገልግሎት የማግኘት፣	t) Accessing 24/7 customs services;
2) የወርቅ ደረጃ ያገኘ የመብቱ ተጠቃሚ ሰው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ከተዘረዘሩት ጥቅሞች በተጨማሪ የሚከተሉት ጥቅሞችን ያገኛል።	**2)** A person who has obtained Gold status as a beneficiary of the right will receive the following additional benefits in addition to those listed in subsection (1):
ሀ) ለቀረጥና ታክስ ክፍያ ያለቅድመ ክፍያ በባንክ/በኢንሹራንስ ዋስትና የመስተናገድ፣	a) Processing duties and taxes payments without prepayment using a bank/insurance guarantee;
ለ)የቦንድድ መጋዘን በራሳቸው የማስተዳደር፣	b) Managing their own bonded warehouse;
3) የፕላቲኒየም ደረጃ ያገኘ የመብቱ	3) A person who has obtained Platinum status

ተጠቃሚ ሰው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) ከተዘረዘሩት ጥቅሞች በተጨማሪ የሚከተሉት ጥቅሞችን ያገኛል።

as a beneficiary of the right will receive the following additional benefits in addition to those listed in subsections (1) and (2):

ሀ) በቋሚነት ድጋፍ የሚያደርግ ባለሙያ የማግኘት፣

a) Access to a dedicated professional for ongoing support;

ለ) የወጪ ዕቃዎችን በራሱ አሽጎ የመላክ፣

b) Independently packing and exporting goods;

13. ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚደረግ ትብብር

13. Cooperation with Other Institutions

ኮሚሽኑ ለፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች የተፈቀደላቸውን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግና የቁጥጥር ሥርዓቱን በጋራ ለማከናወን ከሌሎች አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ጋር በቅርበትና በትብብር መስራት ይጠበቅበታል።

The Commission is expected to work closely and collaboratively with other service-providing institutions to implement the authorized rights for program beneficiaries and jointly execute the control system.

1) ኮሚሽኑ በጉምሩክ ደንብ ቁጥር 518/2014 አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት ሌሎች አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ለፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች ፈጣን አገልግሎት መስጠት የሚያስችል አሰራር ዘርግተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ በቅርበት ይሰራል።

1) Based on Customs Regulation No. 518/2014, Article 14, Subarticle (1), the Commission works closely with other service-providing institutions to establish and implement procedures enabling expedited services for program beneficiaries of the program.

2) ኮሚሽኑ በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው ብቁ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚደረግ የኦዲት ሂደት ከሌሎች በአቅርቦት ሰንሰለቱ ሚና ካላቸው አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ጋር የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል።

2) The Commission exchanges information with other service-providing institutions involved in the supply chain during the audit process to verify the eligibility of individuals applying to join the program.

3) ኮሚሽኑ የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ሰው የተፈቀደለትን መብት ተግባራዊ ለማድረግ ከሌሎች አገልግሎት ሰጭ ተቋማት እና የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ጋር የጋራ ሥምምነት በመፈራረም ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል።

3) The Commission signs joint agreements with other service-providing institutions and trade and sector association councils to implement the authorized rights of program beneficiaries.

4) ኮሚሽኑ የፕሮግራሙን ውጤታማነት

4) The Commission facilitates a permanent

ለማረጋገጥ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ቋሚ የሆነ የምክክር መድረክ ያመቻቻል።

consultation forum with relevant institutions to ensure the program's effectiveness.

5) ኮሚሽኑ የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎችን በተመለከተ መረጃዎችን ወቅታዊ በማድረግ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ለሚመለከታቸው ተቋማት ተደራሽ ያደርጋል።

5) The Commission keeps information about program beneficiaries up to date and makes it accessible to relevant institutions via electronic means.

14. ከሌሎች አገራት የጉምሩክ አስተዳደሮች ጋር ስለሚደረግ ትብብር

14. Cooperation with Customs Administrations of Other Countries

1) ኮሚሽኑ ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾችን በተመለከተ ከሌሎች አገራት የጉምሩክ አስተዳደሮች ጋር የጋራ ስምምነት በመፈፀም ተግባራዊ ያደርጋል።

1) The Commission implements mutual agreements with customs administrations of other countries regarding Authorized Economic Operators (AEOs).

2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አገራችን ተቀብላ ባፀደቃቻቸው የሁለትዮሽ እና የባለብዙ ሥምምነቶች መሰረት ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም ተጠቃሚዎችን ዕውቅና ይሰጣል።

2) Subject to the provisions of sub-article (1) of this article, the country recognizes beneficiaries of the Authorized Economic Operators program based on bilateral and multilateral agreements it has accepted and approved.

15. የስጋት ስራ አመራርን ተግባራዊ ስለማድረግ

15. Implementing Risk Management

ኮሚሽኑ በፕሮግራሙ የተቃፊ ሰው መረጃን የሥጋት ስራ አመራር አሰራርን በመከተል ወቅታዊ ያደርጋል፤ ይተነትናል፤ ያሰራጫል፤ ያስተዳድራል።

The Commission keeps information of persons involved in the program up-to-date, analyzes, disseminates, and manages it by following risk management procedures.

16.የፕሮግራሙ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ግዴታ

16. Obligations of a Program Beneficiary

1) በስጋት ስራ አመራር መርህ መሰረት የገቢም ሆነ ወጪ ዕቃዎች ለፍተሻ እና ሰነድ ምርመራ ሲመረጡ ተባባሪ የመሆን፤

1) Cooperate when import or export goods are selected for inspection and document verification based on risk management principles.

2) የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ሰው በህግ የተሰጠውን መብት አክብሮ የመስራት፤

2) Operate in compliance with the rights granted by law to the program beneficiary.

3) የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ለማከናወን

3) Cooperate in conducting post-clearance

ተባባሪ መሆክና አስፈላጊ ሰነዶችን የማቅረብ፤

4) በጉምሩክ እና በሀገር ውስጥ ገቢ የሚፈለግበትን ክፍያ በወቅቱና በትክክል አሳውቆ የመክፈል፤

5) ከአቅርቦት ሰንሰለት ጋር የተያያዘ ለውጥ ሲኖር በወቅቱ ለኮሚሽኑ የማሳወቅ፤

6) የስራ ቦታ ለውጥ ሲያደርግ ወይም በተለያየ ምክንያት ቢዘጋ በአንድ ወር ጊዮ ውስጥ ለኮሚሽኑ የማሳወቅ፤

7) ከጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ጋር በተያያዘ ጥፋት የፈፀሙ ሰራተኞች ላይ እርምጃ መውሰድ እና ለኮሚሽኑ የማሳወቅ፤

8) በንግድ ሰንሰለት ውስጥ ባለው ተሳትፎ የግንኙነት አግባብን ጤናማነት የመጠበቅ፤

ክፍል አራት

የምስክር ወረቀት ስለማደስ፣ ስለማገድ እና ስለመሰረዝ

17. መሠረቱ

1) ኮሚሽኑ በልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም እንዲታቀፍ የምስክር ወረቀት የሰጠውን ሰው በመመሪያው የተቀመጡ ግዴታዎችን አክብሮ እየሰራ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የተሰጠውን የፕሮግራሙን ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ሊያድስ፣ ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል።

2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ የመብቱ ተጠቃሚ በዚህ መመሪያ የተደነገጉ ግዴታዎችን አክብሮ እየሰራ ያለመሆኑን ሲያምን ይህንኑ እንዲያውቀውና አስፈላጊውን ማስተካከያ

audits and provide necessary documents.

4) Accurately declaring and paying in due time the required customs and domestic revenue fees.

5) Notify the Commission promptly of any changes related to the supply chain.

6) Notify the Commission within one month of any change in workplace or closure for any reason.

7) Take action against employees who commit offenses related to customs procedures and notify the Commission.

8) Maintain the integrity of relationships in the trade chain through participation.

Part Four

Regarding Renewal, Suspension, and Cancellation of Certificates

17. Basis

1) The Commission may renew, suspend, or cancel the certificate of participation in the Authorized Economic Operators program for a person issued a certificate, by conducting appropriate monitoring and control to ensure compliance with the obligations set out in the directive.

2) Subject to the provisions of sub-article (1) of this article, if the Commission believes that the beneficiary is not complying with the obligations set out in this directive, it will notify the beneficiary in writing to make the

እንዲያደርግ ለባለመብቱ በፅሑፍ ያሳውቃል።

necessary corrections.

18. ስለማደስ

1) በዚህ መመሪያ መሰረት የተቀመጡ መስፈርቶችን አሟልቶ የፕሮግራሙ ተጠቃሚ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የምስክር ወረቀቱ የመጠቀሚያ ጊዜ ከመጠናቀቁ ከ3 /ሶስት/ ወር በፊት የይታደስልኝ ጥያቄ ማቅረብ ይኖርበታል። ሆኖም ግን ይህ የጊዜ ገደብ በአሳማኝ ምክንያት ሊራዘም ይችላል።

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት ለቀረበ ጥያቄ የክትትልና ድጋፍ ስራዎችን ሪፖርት መሰረት በማድረግ ያለቅድመ ሁኔታ ሊያድስ ይችላል።

3) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) ድንጋጌ ቢኖርም፡- ሀ) ከፕሮግራሙ ጋር በተያያዘ የሕግና የአሰራር ለውጥ ሲኖር፤ ለ) የመብቱ ተጠቃሚ የተሰጠውን መብት በአግባቡ አለመጠቀሙን አመላካች ሁኔታዎች ሲኖር፤ ሐ) ከሌሎች ተቋማት በሚገኝ መረጃ፤ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) ከፊደል ተራ (ሀ-ሐ) ከተቀመጡት አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ በድጋሚ ኦዲት በማድረግ ሊያድስ ይችላል።

18. Regarding Renewal

1) A person issued a certificate for participation in the program, having met the requirements set out in this directive, must submit a renewal request at least three months before the certificate's validity expires. However, this deadline may be extended for convincing reasons.

2) Based on the request submitted under sub-article (1) of this article, the certificate may be renewed unconditionally based on monitoring and support activity reports.

3) Notwithstanding the provisions of sub-article (2) of this article: a) If there are legal or procedural changes related to the program; b) If there are indications that the beneficiary is not properly exercising the granted rights; c) Based on information from other institutions; The Commission may renew the certificate by conducting a re-audit if any of the conditions listed in sub-article (3) (a-c) are met.

19. ስለማገድ

1) የመብቱ ተጠቃሚ በኢኮኖሚ ወንጀል ተጠርጥሮ የወንጀል ምርመራ እየተከናወነበት ከሆነ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ፤

2) የመብቱ ተጠቃሚን ከፕሮግራሙ ሊያሳግድ የሚችል በቂ ምክንያት መኖሩ በኮሚሽኑ ሲታመንበት ተጣርቶ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ፤

19. Regarding Suspension

1) If the beneficiary is suspected of an economic crime and is under criminal investigation, until a decision is reached;

2) If the Commission believes there is sufficient reason to suspend the beneficiary from the program, until a final decision is reached after verification;

3) በጉምሩክ ወይም በሀገር ውስጥ ገቢ የተጠየቀው የኦዲት ግኝት መጠን በራስ ተነሳሽነት አሳውቆ ከከፈለው ጋር ሲነፃፀር ከ10 በመቶ በላይ ሆኖ በይግባኝ ሥርዓት የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ፤

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተገለጸው ቢኖርም የመብቱ ተጠቃሚ ከተጠረጠረበት ወንጀል ነፃ ከተባለ ዕገዳው ወዲያውኑ ይነሳል።

20. ስለመሰረዝ

ኮሚሽኑ፡-

1) በደንቡና በዚህ መመሪያ መሰረት የሰጠውን የምስክር ወረቀት በሚከተሉት ምክንያቶች ከፕሮግራሙ ተጠቃሚነት ሊሰርዝ ይችላል።

ሀ) በፕሮግራሙ መመዘኛ መስፈርት መሰረት የእድሳት ኦዲት ተደርጎ ብቁ ሆኖ ካልተገኘ፤

ለ) በጉምሩክ ወይም በሀገር ውስጥ ገቢ የተጠየቀው የኦዲት ግኝት መጠን በራስ ተነሳሽነት አሳውቆ ከከፈለው ጋር ሲነፃፀር ከ10 በመቶ በላይ ሆኖ በይግባኝ ሥርዓት የመጨረሻ ውሳኔ የፀና ከሆነ፤

ሐ)የመብቱ ተጠቃሚ በኢኮኖሚ ወንጀል ተጠርጥሮ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ፤

መ)የመብቱ ተጠቃሚ በተለያየ ምክንያት ህልውናውን ካጣ፣

ሠ)የመብቱ ተጠቃሚ በፕሮግራሙ ተጠቃሚ ሆኖ እንደማይቀጥል በራሱ ማመልከቻ ለኮሚሽኑ ካሳወቀ

ረ) ኮሚሽኑ የፕሮግራሙን ተጠቃሚ ፈቃድ ሊያሰርዝ የሚችል ምክንያት መኖሩን በበቂ ምክንያት ካረጋገጠ፤

3) If the audit findings requested by customs or domestic revenue exceed 10 percent of the voluntarily reported and paid amount, until a final decision is made through the appeal process;

4) Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this article, if the beneficiary is declared clear of the suspected crime, the suspension is lifted immediately.

20. Regarding Cancellation

The Commission:

1) may cancel the certificate of participation in the program for the following reasons:

a) If a renewal audit conducted based on the program's criteria finds the beneficiary unqualified;

b) If the audit findings requested by customs or domestic revenue exceed 10 percent of the voluntarily reported and paid amount, and a final decision is upheld through the appeal process;

c) If the beneficiary is suspected of an economic crime and found guilty of the charged offense;

d) If the beneficiary ceases to exist for various reasons;

e) If the beneficiary notifies the Commission in writing that they will not continue as a program participant;

f) If the Commission confirms with sufficient reason that there is a basis to cancel the beneficiary's authorization.

2) በዚህ መመሪያ መሰረት የተቀመጡ መስፈርቶችን ባለማሟላት ጥያቄው ውድቅ የተደረገ ድርጅት ከአንድ ዓመት በኋላ በፕሮግራሙ ለመታቀፍ እንደገና ማመልከት ይችላል።

2) An organization whose application is rejected for failing to meet the requirements set out in this directive may reapply for the program after one year.

3) በዚህ መመሪያ መሰረት የተጠቃሚነት መብቱ የተሰረዘበት ሰው ዳግም በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ማመልከት የሚችለው ከተሰረዘበት ከሶስት ዓመት በኋላ ነው።

3) A person whose participation rights have been canceled under this directive can reapply for the program after three years from the date of cancellation.

4) በዚህ አንቀጽ በተገለጹት ምክንያቶችና ሁኔታዎች የመብቱ ተጠቃሚዎች ፈቃድ የሚሰረዘው በኮሚሽነሩ ውሳኔ እና ፊርማ ይሆናል።

4) The cancellation of a beneficiary's authorization under the reasons and conditions specified in this article shall be made by the decision and signature of the Commissioner.

21. የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

21. Complaint Submission System

1) ለፕሮግራሙ ተጠቃሚ የተሰጠ የልዩ መብት ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት በዚህ መመሪያ መሰረት ካልታገደ ወይም ካልተሰረዘ በስተቀር የምስክር ወረቀቱ በመጠቀሚያ ጊዜው ውስጥ ፀንቶ ይቆያል።

1) Unless suspended or revoked in accordance with this directive, the certificate of entitlement granted to a program beneficiary remains valid during its usage period.

2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘ ማንኛውም ሰው ከዚህ በታች በተጠቀሱት ምክንያቶች ቅሬታ ሊያቀርብ ይችላል፦

2) Subject to the provisions of sub-article (1) of this article, any person may submit a complaint for the following reasons in connection with this directive:

ሀ) በቅድመ ኦዲት እና በዝርዝር ኦዲት መሰረት ለቀረበ ጥያቄ በኮሚሽኑ ውሳኔ ማመልከቻው ውድቅ የተደረገ እንደሆነ፤

a) If an application is rejected by the Commission's decision based on a preliminary audit and detailed audit;

ለ) በዚህ መመሪያ በአንቀፅ 15 ላይ ለመብቱ ተጠቃሚዎች የተዘረዘሩት ጥቅሞች አተገባበር ላይ ቅር የተሰኘ እንደሆነ፤

b) If dissatisfied with the implementation of the benefits listed for beneficiaries under Article 15 of this directive;

ሐ) በዚህ መመሪያ አንቀፅ 20 እና 21

c) If a person whose entitlement is suspended or revoked under Articles 20 and 21 of this

መሰረት የመጠቀሚያ መብቱ የታገደ ወይም የተሰረዘበት ሰው ውሳኔውን የተቃወመ እንደሆነ፤

directive objects to the decision.

22. ቅሬታ ስለመቀበልና ውሳኔ ስለመስጠት

22. Receiving Complaints and Issuing Decisions

1) ኮሚሽኑ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 22 መሰረት የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በመቀበል ውሳኔ በፅሁፍ ይሰጣል።

1) The Commission shall receive complaints submitted under Article 22 of this directive and issue decisions in writing.

2) በዚህ መመሪያ አንቀፅ 22 ንዑስ አንቀፅ 2(ሀ) መሰረት ፕሮግራሙ ተጠሪ በሆነበት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ውሳኔ በፅሁፍ ይሰጣል።

2) For complaints submitted under Article 22, sub-article 2(a) of this directive, the Directorate Director responsible for the program shall issue a decision in writing.

3) በዚህ መመሪያ አንቀፅ 22 ንዑስ አንቀፅ 2(ለ) መሰረት የሚቀርብ ቅሬታ ፕሮግራሙ ተጠሪ በሆነበት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አስፈላጊውን ማጣራት ተደርጎ ውሳኔ በፅሁፍ ይሰጣል።

3) For complaints submitted under Article 22, sub-article 2(b) of this directive, the Directorate Director responsible for the program shall conduct the necessary review and issue a decision in writing.

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ (2) እና (3) በተሰጠ ውሳኔ ያልረካ የመብቱ ተጠቃሚ ቅሬታውን ለጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት ማቅረብ ይችላል። ዳይሬክቶሬቱም የቀረበለትን አቤቱታ አጣርቶ ውሳኔ በፅሁፍ ይሰጣል።

4) A beneficiary dissatisfied with a decision issued under sub-articles (2) and (3) of this article may submit their complaint to the Customs Complaint Review Directorate, which shall review the complaint and issue a decision in writing.

5) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2(ሐ) በተሰጠ ውሳኔ ያልረካ እንደሆነ ቅሬታውን ለጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፤ ዳይሬክቶሬቱም አጣርቶ የውሳኔ ሃሳብ ለኮሚሽነሩ ያቀርባል።

5) If dissatisfied with a decision issued under sub-article 2(c) of this article, the complaint shall be submitted to the Customs Complaint Review Directorate, which shall review and submit a decision proposal to the Commissioner.

6) በዚህ አንቀፅ መሰረት በኮሚሽነሩ የተሰጠ

6) The decision issued by the Commissioner

ውሳኔ የኮሚሽኑ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል።

under this article shall be the final decision of the Commission.

7) በኮሚሽኑ የመጨረሻ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል ጉዳዩን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

7) An entity dissatisfied with the Commission's final decision may submit the matter to a competent court.

23. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር ተፈርሞ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ እንዲሁም በገቢዎችና በፍትህ ሚኒስቴር ድህረ ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

23. Effective Date of the Directive

This directive shall come into force from the date it is signed by the Minister of Revenues, registered with the Ministry of Justice, and posted on the websites of the Ministry of Revenues and the Ministry of Justice.

አዲስ አበባ፤ ግንቦት 2017 ዓ.ም

Addis Ababa; May 2025

አይናለም ንጉሴ አሊ
የገቢዎች ሚንስቴር ሚኒስትር

Aynalem Nigussie Ali
Minister, Ministry of Revenues

ተቀጽላ አንድ	**Appendix One**
ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም ለመታቀፍ የማመልከቻ መጠየቅያ ቅጽ	Application Form for Authorized Economic Operators Program Participation
መጀመሪያ ማመልከቻ □ ዕድሳት □ ለማራዘም □	Initial Application □ Renewal □ Extension □
1. የአመልካች ድርጅት ሥም	1. Name of the Applicant Organization
2. የአመልካች ድርጅት ህጋዊ መሰረት/ ደረጃ (ኢ.ማ፣ ኃላ/የተ/የግ/ማ...)	2. Legal Basis/Status of the Applicant Organization (PLC, LLC, Partnership, etc.)
3. የተቋቋመበት ጊዜ	3. Date of Establishment
4. የድርጅቱ ዋና መ/ቤት አድራሻ (ስ.ቁ፤ የፋክስ. ቁ እና ኢ.ሜይል)	4. Main Office Address of the Organization (Phone No., Fax No., and Email)
5. የድርጅቱ ዋና ዋና መጋዘኖች እና ፋብሪካ መገኛ አድራሻ	5. Location Address of the Organization's Main Warehouses and Factories
6. የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ (ሥም፣ ስ.ቁ እና ኢ.ሜይል)	6. Main Manager of the Organization (Name, Phone No., and Email)
7. የተሰማራበት የሥራ ዘርፍ	7. Sector of Operation
8. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር	8. Taxpayer Identification Number
9. የድርጅቱ የጉምሩክ ወኪል ሥም	9. Name of the Organization's Customs Agent
10. የጉምሩክ ወኪሉ የቢሮ እና ተንቀሳቃሽ ስልክ ቁጥር	10. Office and Mobile Phone Numbers of the Customs Agent
11. የሚያስመጣቸው/የሚያመርታቸው ዋና ዋና ዕቃዎች	11. Main Goods Imported/Produced
12. የድርጅቱ ፋብሪካዎችና መጋዘኖች አድራሻ	12. Address of the Organization's Factories and Warehouses
13. የአገር ውስጥ ግብር የታክስ ማዕከል (ቅ/ፅ/ቤት)	13. Domestic Tax Revenue Center (Branch/Sub-City Office)
14. ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት የዘረጋው መረጃ ቴክኖሎጂ ዓይነት	14. Type of Information Technology System Used for Internal Control
15. የመረጃ ቴክኖሎጂው የሚያስተሳስራቸው የሥራ ክፍሎች	15. Work Units Linked by the Information Technology System
16. የአባሪዎች ብዛት	16. Number of attachments
17. የሚስተናገድባቸው የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች	17. Customs Branch Offices Where Services Are Processed
ከላይ የተገለጹት መረጃዎች በሙሉ ትክክል መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ.	I confirm with my signature that all the information provided above is accurate.
ፊርማ..	Signature......................................
ቀን..	Date..
ሥም...	Name..
ኃላፊነት....................................	Responsibility.................................

ተቀጽላ ሁለት	Appendix Two
በአስመጪ፣ በአምራች እና በላኪ የስራ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች የህግ ተገዥነት እና የውስጥ አሰራር ኦዲት ዝርዝር የመመዘኛ መስፈርቶች እና የመለኪያ ነጥቦች	Detailed compliance and internal process audit criteria and measurement points for companies engaged in import, manufacturing, and export sectors
1. የህግ ተገዥነት ታሪክ ------ 35%	**1. Legal Compliance History ------ 35%**
1.1. በጉምሩክ ያለው የሕግ ተገዥነት ታሪክ	1.1. Legal Compliance History in Customs
ሀ) በድህረ እቃ አወጣጥ የኦዲት ግኝት መጠን 10	a) Audit finding rate in post-clearance ……………………..10
ለ) በዕቃ አወጣጥ ሂደት የተከፈለ ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ መጠን......6	b) Additional duties and taxes paid during clearance process……6
ሐ) ልዩነት የተገኘባቸው ሰነዶች በመቶኛ.... 5	c) Percentage of documents with discrepancies... 5
መ) ከጉምሩክ ሥነ-ስርዓት አፈፃፀም ጋር በተገናኘ የአሰራር ጥሰት 4	d) Operational errors related to customs system performance ……4
1.2. በአገር ውስጥ ታክስ ያለው የሕግ ተገዥነት ታሪክ	**1.2. Legal Compliance History in Domestic Taxation**
ሀ) ዓመታዊ ግብርን በፈቃደኝነት አሳውቆ የመክፈል ሁኔታ 2	a) Voluntary declaration and payment status of annual tax ………….. .2
ለ) የኦዲት ግኝት መጠን ከከፈለው ዓመታዊ ግብር አንፃር 5	b) Audit finding rate relative to paid annual tax …..………… 5
ሐ) በአገር ውስጥ ገቢ ያለው የሕግ ተገዥነት ደረጃ 3	c) Level of compliance with domestic income tax …………...……….. 3
2. ለአገር ኢኮኖሚ ያለው አስተዋፅዖ -- 20%	**2. Contribution to the National Economy --20%**
ሀ) የተከፈለ የቀረጥና ታክስ መጠን......... 5	a) Amount of duties and taxes paid …………… 5
ለ) የተከፈለ የአገር ውስጥ ገቢ መጠን.........5	b) Amount of domestic income paid …..……...5
ሐ) የፈጠረው የሥራ ዕድል..................... 6	c) Employment opportunities created ……....... 6
መ) በማኅበራዊ ድጋፎች ያለው ተሳትፎ.....4	d) Participation in social support programs …….4
3. የሃብት አመራር እና የውስጥ የቁጥጥር ሥርዓት ----------------------- 15%	**3. Asset Management and Internal Control System ---------------------- 15%**
ሀ)የውስጥ አሰራር ሥርዓት................. 8	a) Internal operational system ……………….. 8
ለ) በዕቅድ የመመራት ባህል............. 4	b) Culture of planning and guidance ………….. 4
ሐ) የሥልጠና አሰጣጥ ሁኔታ.............. 3	c) Training provision status ………………….. 3
4. መረጃ ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ----10%	**4. Information Technology Infrastructure Development ------------ 10%**
ሀ) የመረጃ ቴክኖሎጂ ትስስር ሁኔታ......... 4	a) IT connectivity status …...……………... 4
ለ) የመረጃ ቴክኖሎጂ ደህንነት ሁኔታ....... 3	b) IT security status …….……………..... 3
ሐ)የመረጃ ቴክኖሎጂን የማስተዳደር ሁኔታ--3	c) IT management status …..… 3
5. የጥንቃቄና ደህንነት መስፈርቶች---- 10%	**5. Safety and Security Standards --------- 10%**
ሀ) የድርጅቱ ቅጥር ግቢ እና መጋዘን ደህንነት ሁኔታ 4	a) Security status of company premises and warehouse ……………... 4
ለ) የመረጃ ደህንነት 3	b) Information security ……….…………….3
ሐ) የሰራተኛ ደህንነት 3	c) Employee safety ………….………………3
6. የፋይናንስ አቅም ----------------------- 10%	**6. Financial Capacity ------------------------ 10%**
ሀ) የሽያጭ መጠን 4	a) Sales volume ………………………………..4
ለ) የተጣራ ትርፍ 3	b) Net profit ……………………………........3
ሐ) የትርፋማነት መለኪያ 3	c) Profitability measure ………………………3

ተ.ቁ	ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም ለመታቀፍ የመገምገሚያ ቅጽ	Evaluation Form for Participation in the Special Economic Operators Program	Points Allocated
1	**የህግ ተገዥነት ታሪክ**	**Legal Compliance History**	35%
1.1	**በጉምሩክ የህግ ተገዥነት ታሪክ**	**Customs Legal Compliance History**	25%
1.1.1	**በድህረ እቃ አወጣጥ የኦዲት ግኝት መጠን**	**Audit Finding Rate in Post-Clearance Audit**	10%
	የኦዲት ግኝት መጠን እስከ 5% ከሆነ	Audit finding rate ≤ 5%	10
	ኦዲት ያልተደረገ እና የስጋት ደረጃው ዝቅተኛ/መካከለኛ ከሆነ	No audit conducted and risk level is low/medium	8
	የኦዲት ግኝት መጠን ከ5.1% እስከ 8% ከሆነ	Audit finding rate 5.1% – 8%	6
	የኦዲት ግኝት መጠን ከ8.1% እስከ 12% ከሆነ	Audit finding rate 8.1% – 12%	5
	የኦዲት ግኝት መጠን ከ12.1% እስከ 150% ከሆነ	Audit finding rate 12.1% – 150%	4
1.1.2	**በዕቃ አወጣጥ ዳግም ማጣራት ሂደት የተከፈለ ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ መጠን**	**Additional Duties & Taxes Paid During Re-inspection**	6%
	እስከ 2.5%	≤ 2.5%	6
	2.51% - 4%	2.51% – 4%	5
	4.1% - 6%	4.1% – 6%	4
	ከ6.1% በላይ	> 6.1%	3
1.1.3	**በዕቃ አወጣጥ ዳግም ማጣራት ልዩነት የተገኘባቸው ሰነዶች በመቶኛ**	**Discrepancy Rate in Documents During Re-inspection**	5%
	እስከ 5%	≤ 5%	5
	5% - 10%	5% – 10%	4
	10% - 15%	10% – 15%	3
	15% - 20%	15% – 20%	2
1.1.4	**ከጉምሩክ ሥነ-ስርዓት አፈፃፀም ጋር በተገናኘ የአሰራር ጥሰት**	**Operational Errors Related to Customs Procedures**	4%
	ባለፉት 3 ዓመታት ያልተፈፀመ	No errors in past 3 years	4
1.2	**በአገር ውስጥ ገቢ የህግ ተገዥነት ታሪክ**	**Domestic Revenue Legal Compliance History**	10%
1.2.1	**ዓመታዊ ግብርን በወቅቱ እና በፈቃደኝነት አሳውቆ የመክፈል ሁኔታ**	**Timely & Voluntary Tax Declaration & Payment**	2%
	በፈቃደኝነትና በወቅቱ የሚከፍል	Pays voluntarily & on time	2
	በወቅቱ ባለመክፈሉ በቅጣት የተስተናገደ	Pays late with penalties	1
1.2.2	**ባለፉት 3 ዓመታት የኦዲት ግኝት መጠን ከፈለው ግብር አንፃር**	**Audit Finding Rate Over Past 3 Years**	5%
	እስከ 5%	≤ 5%	5
	ኦዲት ያልተደረገ እና የስጋት ደረጃ መካከለኛ/ዝቅተኛ	No audit, medium/low risk	4
	5.1% - 10%	5.1% – 10%	3
	ኦዲት ያልተደረገ እና የስጋት ደረጃ ከፍተኛ	No audit, high risk	2
	10.1% - 15%	10.1% – 15%	1
2	**ለአገር ኢኮኖሚ �ስተዋፅዖ**	**Contribution to National Economy**	20%
2.1	**ባለፉት 3 ዓመታት የተከፈለ የቀረጥና ታክስ መጠን**	**Duties & Taxes Paid (Past 3 Years)**	5%

	> 1.2 ቢሊዮን ብር	> 1.2 billion ETB	**5**
	900 ሚሊዮን - 1.19 ቢሊዮን ብር	900M – 1.19B ETB	**4**
	600 ሚሊዮን - 899.99 ሚሊዮን ብር	600M – 899.99M ETB	**3**
	< 600 ሚሊዮን ብር	< 600M ETB	**2**
2.2	**ባለፉት 3 ዓመታት የተከፈለ የአገር ውስጥ የትርፍ ግብር**	**Domestic Profit Tax Paid (Past 3 Years)**	**5%**
	> 200 ሚሊዮን ብር	> 200M ETB	**5**
	150 ሚሊዮን - 199.99 ሚሊዮን ብር	150M – 199.99M ETB	**4**
	100 ሚሊዮን - 149.99 ሚሊዮን ብር	100M – 149.99M ETB	**3**
	< 100 ሚሊዮን ብር	< 100M ETB	**2**
አምራች	**አመልካች ድርጅቱ አምራች፣ የቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ተጠቃሚ ወይም የግብር እፎይታ ላይ ከሆነ**	**If applicant is a manufacturer, duty-free incentive beneficiary, or tax incentive beneficiary**	**10%**
	> 500 ሚሊዮን ብር	> 500M ETB	**10**
	350 ሚሊዮን - 499.99 ሚሊዮን ብር	350M – 499.99M ETB	**8**
	250 ሚሊዮን - 349.99 ሚሊዮን ብር	250M – 349.99M ETB	**6**
	100 ሚሊዮን - 249.99 ሚሊዮን ብር	100M – 249.99M ETB	**4**
	< 100 ሚሊዮን ብር	< 100M ETB	**2**
ላኪ	**ባለፉት 3 ዓመታት ያስገኘው የውጭ ምንዛሬ መጠን**	**Foreign Exchange Earnings (Past 3 Years)**	**5%**
	> 150 ሚሊዮን ዶላር	> 150M USD	**5**
	100 ሚሊዮን - 149.99 ሚሊዮን ዶላር	100M – 149.99M USD	**4**
	50 ሚሊዮን - 99.99 ሚሊዮን ዶላር	50M – 99.99M USD	**3**
	< 50 ሚሊዮን ዶላር	< 50M USD	**2**
2.3	**የፈጠረው የስራ እድል (በፔይሮል ሰነዶች የተረጋገጠ)**	**Employment Creation (Verified by Payroll)**	**6%**
	> 300 ሰራተኞች	> 300 employees	**6**
	250 - 299 ሰራተኞች	250 – 299 employees	**5**
	200 - 249 ሰራተኞች	200 – 249 employees	**4**
	150 - 199 ሰራተኞች	150 – 199 employees	**3**
	< 150 ሰራተኞች	< 150 employees	**2**
2.4	**በማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ያደረገው አስተዋጽኦ**	**Contribution to Social Causes**	**3%**
	ማስረጃ ካቀረበ	With documented proof	**4**
3	**የሃብት አመራር እና የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት**	**Asset Management & Internal Control System**	**15%**
3.1	**የውስጥ የአሰራር ስርዓት**	**Internal Operational System**	**8%**
	ለሁሉም የስራ ክፍሎች የፀደቀ ስርዓት ያለው	Approved system for all departments	**8**
	ለዋና ዋና ክፍሎች የፀደቀ ስርዓት ያለው	Approved system for major departments	**6**
	በቅፅ ብቻ የሚከታተል	Follow-up only in forms	**4**
3.2	**በእቅድ የመመራት ባህል**	**Planning Culture**	**4%**
	3+ ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ያለው	Has 3+ year strategic plan	**4**
	ዓመታዊ እቅድ ያለው	Has annual plan	**3**

3.3	**የስልጠና አሰጣጥ ሁኔታ**	**Training Provision Status**	3%
	በሎጂስቲክስ፣ ጉምሩክ፣ ታክስ ስልጠና ያቀርባል	Provides logistics, customs, tax training	3
	በሎጂስቲክስ ስልጠና ያቀርባል	Provides logistics training	2
4	**የመረጃ ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማትና አጠቃቀም**	**IT Infrastructure Development & Utilization**	10%
4.1	**የመረጃ ቴክኖሎጂ ትስስር ሁኔታ**	**IT Integration Status**	4%
	ሁሉንም ክፍሎች የሚያገናኝ	Integrates all departments	4
	ዋና ክፍሎችን (ፋይናንስ፣ መጋዘን) የሚያገናኝ	Integrates major departments (finance, warehouse)	3
	ፋይናንስና መጋዘን ብቻ የሚያገናኝ	Integrates only finance & warehouse	2
	ፋይናንስ/መጋዘን የተለዩ ስርዓቶች አሉት	Separate systems for finance/warehouse	1
4.2	**የመረጃ ቴክኖሎጂ ደህንነት ሁኔታ**	**IT Security Status**	3%
	- ደህንነት ስርዓት፣ ፋየርዎል፣ አንቲቫይረስ፣ ዲዛስተር ሪከቨሪ ባክአፕ	Security system, firewall, antivirus, disaster recovery backup	3
	- ፋየርዎል፣ አንቲቫይረስ፣ ዳታ ማዕከል	Firewall, antivirus, data center	2
	- ፋየርዎልና አንቲቫይረስ ብቻ	Only firewall & antivirus	1
4.3	**የመረጃ ቴክኖሎጂ የማስተዳደር ሁኔታ**	**IT Management Status**	3%
	ራሱን የቻለ የIT ክፍል አለው	Dedicated IT department	3
	በባለሙያ የሚተዳደር	Managed by professional	2
	በኮንትራት ሰራተኛ	Managed by contractor	1
5	**የጥንቃቄና ደህንነት መስፈርቶች**	**Safety & Security Standards**	10%
5.1	**የድርጅቱ ቅጥር ግቢ እና መጋዘን ደህንነት**	**Premises & Warehouse Security**	4%
	- አጥር፣ የቁጥጥር በሮች፣ CCTV፣ መጋዘን	Fenced, controlled gates, CCTV, organized warehouse	4
	- አጥር፣ በሮች፣ CCTV	Fenced, gates, CCTV	3
	- አጥርና በሮች ብቻ	Only fence & gates	2
5.2	**የመረጃ ደህንነት ሁኔታ**	**Data Security Status**	3%
	- IT-በዕድቅ የተያዘ፣ የሰነድ ማስቀመጫ ክፍል	IT-based system, dedicated document storage	3
	- አስተማማኝ የሰነድ ስርዓት፣ ማስቀመጫ ክፍል	Reliable doc system, storage	2
	- አስተማማኝ የሰነድ ስርዓት	Reliable doc system	1
5.3	**የሰራተኛ ደህንነት**	**Employee Safety**	3%
	- ኢንሹራንስ፣ የደህንነት ህጎች፣ መጠበቂያ ቁሳቁሶች	Insurance, safety rules, equipment	3
	- የደህንነት ህጎች፣ ቁሳቁሶች	Safety rules, equipment	2
	- መጠበቂያ ቁሳቁሶች ብቻ	Only safety equipment	1
6	**የፋይናንስ አቅም**	**Financial Capacity**	10%
6.1	**የሽያጭ መጠን (ባለፉት 3 ዓመታት)**	**Sales Volume (Past 3 Years)**	4%
አስመጪ	> 3 ቢሊዮን ብር	> 3B ETB	4
	2-2.99 ቢሊዮን ብር	2B–2.99B ETB	3
	1-1.99 ቢሊዮን ብር	1B–1.99B ETB	2
	< 1 ቢሊዮን ብር	< 1B ETB	1
አምራች/ላኪ	> 2 ቢሊዮን ብር	> 2B ETB	4
	1.5-1.99 ቢሊዮን ብር	1.5B–1.99B ETB	3

	1-1.49 ቢሊዮን ብር	1B–1.49B ETB	2
	< 1 ቢሊዮን ብር	< 1B ETB	1
6.2	**የተጣራ ትርፍ (ባለፉት 3 ዓመታት)**	**Net Profit (Past 3 Years)**	**3%**
	> 450 ሚሊዮን ብር	> 450M ETB	3
	300-449.99 ሚሊዮን ብር	300M–449.99M ETB	2
	< 300 ሚሊዮን ብር	< 300M ETB	1
6.3	**የትርፋማነት አመልካች (በመቶኛ)**	**Profitability Index (%)**	**3%**
	> 20%	> 20%	3
	15%-19.99%	15%–19.99%	2
	< 15%	< 15%	1
አማራጭ	**ድርጅቱ የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ላይ ከሆነ**	**If under Expansion**	**6%**
	> 400 ሚሊዮን ብር	> 400M ETB	6
	300-399.99 ሚሊዮን ብር	300M–399.99M ETB	5
	200-299.99 ሚሊዮን ብር	200M–299.99M ETB	4
	100-199.99 ሚሊዮን ብር	100M–199.99M ETB	3
	< 100 ሚሊዮን ብር	< 100M ETB	2
አማራጭ	**ድርጅቱ የግብር እፎይታ ላይ ከሆነ**	**If under Tax Holiday**	**6%**
	> 2.3 ቢሊዮን ብር	> 2.3B ETB	6
	1.8-2.29 ቢሊዮን ብር	1.8B–2.29B ETB	5
	1.3-1.79 ቢሊዮን ብር	1.3B–1.79B ETB	4
	800 ሚሊዮን-1.29 ቢሊዮን ብር	800M–1.29B ETB	3
	< 800 ሚሊዮን ብር	< 800M ETB	2
ልዩ ማበረታቻ	**ተጨማሪ ነጥብ የሚያስገኙ ዘርፎች**	**Additional Points for Sectors**	
	በመድኃኒት/ህክምና መሳሪያዎች አምራች	Medicine/medical equipment manufacturer	+5
	አስመጪ + አምራች + ላኪ (ሶስቱም)	Importer + manufacturer + exporter	+3
አጠቃላይ	**የመለኪያ ነጥብ ድምር**	**Total Assessment Score**	**100%**